# ህወሓት ትኩሳት ነው፣ ነቀርሶቹ ሌሎች!

ክፍል ፪

ልዩ ማስጠንቀቂያ! አዎን ማስጠንቀቂያ!

የኢትዮጵያውያንን ቆርጦ መነሳት በመረዳት አንዳንድ የምዕራባውያን ጋዜጦች በ፱ ወሩ ዕልቂታችንን ማወጣጣቸውን እያየን ነው።

( አንድም የምዕራባውያን ዋና የቴሌ ቪዝን ጣቢያ ለሕዝብ ማድረሱን አላየሁም።) ኾኖም ጋዜጣውን አይተው አንዳንድ መንግሥታት ሊሸመግሉ ልበል ሊሸነግሉ መጀመራቸው ይሰማል፤ ፡ አይቀሬ ነው። ከቅምጦቻቸው እጅ መወጣታችንን አይፈልጉምና!

ያቀዱብን ሙሉ በሙለ ገና አልተሳካላቸውም። ይህም የኢትዮጵያ አምላክ በየጊዜው በደነቀረባቸው እንቅፋት ምክንያት ነው። ለወደፊቱ ይዘረዘራል። እንግዲህ እዚህ ከደርስን ማስጨንገፉ የኛ ግዴታ ነው። ባኹኑ ጊዜ ይኽንን ሽንገላ የሚቀበልና ትግሉን ሊያዳክም የሚፈልግ “ መሪ ነኝ !“ ባይ ቢሞክር ባላፈውና ባኹኑ መፍሰስ ላይ ባለው የወገን ደም ተጠያቂ መኾኑን ፡ ይወቅ። በዘመኑ አነገገር ከዚህ ቀደም የተሸወድነው “ ይበቃል!!!”

ለወጣቶች አደራ የሞላበት ማሳሰቢያ !

*ጠላቶቻችሁን ካላወቃችሁ ባለማወቅ ( ሆድ-አደሮች እያወቁ ይገዙላቸዋልና!) የጠላት መሣሪያ እንዳትኾኑ በመጠኑም ቢኾን እንድታውቁ የምፈልገውን በጥሞና አንብቡልኝ። ኢትዮጵያችን ነገ የእናንተ እንድትኾንና በክብር ያቆዩልንን በክብር ለማስተላለፍ እንድትችሉ። የኔ ትውልድ ትንሽ የሚቀድሙኝና የተከተሉኝም ግዴታችንን ባለመወጣታችን አገራችንን ለዚህ ውርደት ወገናችንንም ለሰቆቃ ዳርገናል። ይህ እንዳይቀጥል መበርታት አለብን! አለባችሁ! ስለዚህ ያላኝን ተካፈሉኝ !!*

ትኩሳት የበሽታ ምልክት እንጂ በሽታ አይደለም ይባላል። ራሴን በምሳሌነት ላቅርብ። በ፺፰ - ፺፱ ዓም የኾነ ነው።

ቫሊንበርግ ከሚባሉ የስዊድን ተወላጅና ቤተሰባቸው ጋር ወዳጆች ነበርን። እኝህ አዛውንት ያገራችን ከፍተኛው ፍ/ቤት ፕሬዜዳንት ነበሩ። በጭውውት አደን መውደዴን ነግሬያቸው ነበርና ት/ቢት ለክረምት ሲዘጋ መከፈቻው አቅራቢያ ወደ ጊቤ ሌሎችን ጨምረን ሄድን። ትም/ቤተ እንደተመለስሁ ኃይለኛ ትኩሳት ይዞኝ ወደቤት ተደውሎ እናቴ ፦ መሬት ይቅለላትና! መጥታ ፖ/ቤቱ አጠገብ ወዳለው አንድ የኢጣሊያን ሐኪም ወሰደችኝ። የራስ ምታቱ ነገር አይነሳ፦ ትኩሳቱም የራሴን እጅ እስከሚያቃጥል ነበር።

ሐኪሙም አስፈላጊውን ምርመራ ካደረገ በኋላ ደም ወስዶ የምርመራው ውጤት ሳይመጣለት የወባ መድሃኒት ሰጠኝ። ሌሊቱንም ስትመታን አደረች። ከዚያ ተነቅላ ጠፋች። እዚህ ላይ ትኩሳቱ የበሽታው ምልክትነቱን ልብ በሉ.

እኛም ያገራችንን ነቀርሶች ( ለነቀርሶች ለብዙዎቹ መድሃኒት ተገኝቶ በሃብታሞች የሚታዘዙ መንግሥታት እንዳይወጡ ማደረጋቸውን - የሐኪሞችንና አኹን ያሉትን ባለፋብሪካዎች ጥቅም ለመጠበቅ ማድረጋቸው ይነበባል)

ያገራችንንም ነቀርሶች በገራችን ሕልውና ላይ እንዳሻቸው የሚዳክሩትንና የሚያሰቃዩንን ቅምጦች/ትኩሳቶች ለመጨረሻ ጊዜ እንድንገላገል መድሃኒቱ በጃችን ነውና፦ እንበርታ!
ነቀርሳዎቹ እስቲ ምን ምን እንደበደሉን ልጠቃቅስ። እስከ እምዬ ምኒልክ አላተደፈርንም።

“ነገር ከሥሩ - ውሃ ከጥሩ” እንደሚባለው፦ ፲፬ ያውሮፓ መንግሥታት አፍሪካን ለመቀራመትና በቅርምቱም እርስ - በርሳቸው እንዳይጋጩ በርሊን ላይ በ1884 - 85 ተሰበሰቡ።

እምዬ ምኒልክ ስለዚህ ጉዳዩን ቀደም ብለው ሰምተው ኖሮ በ1891 ( የፈረንጅ) ለእንግሊዟ ንግሥት ቪክቶሪያ ከዚህ የሚከተለውን ጻፉ፦

“ ...የሩቅ አገር ኃያላን አፍሪካን ሲቀራመትዋት የግድ-የለሽነት ተመልካች ልኾን አልሻም ። ኢትዮጵ ያ ላለፉት 14 ምዕተ - ዓለም በአሕዛብ ባሕር ውስጥ የክርስትና ደሴት ኾና ኖራለች። እስካኹን ድረስ ኃያሉ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ጠብቆ አኑሯታል። ለወደፊቱም አስፍቶ እንደሚጠብቃት ተስፋ አለኝ ። ኢትዮጵያን ሊሎቹ ኃያላን ይከፋፍሏታል የሚል ቅንጣት ስጋት የለኝም። በማለት የክርስቲያንዋን ንግሥት ድጋፍ ጠየቁ።

እዚህ ላይ ለማስታወስ የምፈልገው ኢትዮጵያ በግራኝ መሐመድ የደረሰባትን ጥፋት ኹለዬም በማሰብ የክርስቲያን ነገሥታት ይተባበሩናል በሚል እምነት እንደነበረ ነው። እምዬ ምኒልክ ለአውሮፓ ነገሥታት በጻፉት ኹሉ ይህን ነጥብ አበክረው ያነሱት ነበር። እንደርሳቸው ዕምነት ክርስቲያን ክርስቲያንን መርዳት አለበት በማለት ነበር። ግን እያደር ጎልቶ እንደታየው ጥቅማቸውን እንጂ እንኳን ሃይማኖታቸውን ወድደው የገቡትን ቃላቸውን የሚያከብሩ አልነበሩም።

ከአድዋ ጦርነት ኹለት ዓመት በፊት በምዕራብ አፍሪካ ከሰሃራ ደቡብ ያሉት አገሮች ኹሉ ፈረንጆች ቅዱስ መጽሐፍን ይዘው ሲመጡ በአፍሪካውያን ባህል ቤታቸውን ለቀቀው ሲያስተንግድኍቸው። የመጽሕፍ ቅዱስን ትምሕርትን ሲወድዱ ያገሬው ሰዎች ባህላቸውን እንዲረሱ ባላባቶቻቸውን እንዳይታዘዙ ሽማግሌዎቻቸውን እንዳይሰሙ አድርገው ሲቦጠቡጧቸው ስለኢትዮጵያ ይሰሙ ነበርና ‘ “ኢትዮጵያዊነት! “ ብለው ተነስተው ቅኝ ገዥዎችን መሠረት እስከ ደቡብ አፍሪካ አናግተውት እንደነበር አንብቤአለሁ፤፡ አድዋ የመጣው ከዚህ ኹለት ዓመት በኋላ ነው። መነሻው ይሄ መኾኑን ግን አላየሁም፤፡ ጥርጣሬየ ግን “ ነው!”

ከዚያ አድዋ መጣ ! ስለአድዋ ብዙ ተብሏልና ልለፈው። ብዙ ሰው “ ለአፍሪካ ነጻነት...” ይላል። ግን ነው ወይ? የካሪቢያን ደሴቶችና ደቡብ አሜሪካን በማን ማን ሥር ነበሩ? ሰሜን አሚረካስ? አኹን

3 - በመካከለኛው ምሥራቅነት የምትታወቀውና ከእስያስ ስንቶቹ ነበሩ ነጻነት የነበራቸው? አብዛኛዎቹ ከኹለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ነው ነጻነታቸውን ያገኙት። ለዚህ ኹሉ አር አያ የኾነችው፦ የነጻነት ፋና የወጋችው እናታችን በረች። ይህ ኹሉ ነቀርሳ ፈጠረብን፤፡ እንድታውቁት ያህል ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ለዳቧቸው በቂ ስንዴ የነበራት ፈረንሳይ ብቻ ነበረች። በዚህ ላይ ለቤት አሽከርነት ለጓሮ ኮትኳችነት ለመንገድ - ድልድይ ለባቡር ሃዲድ .... ባጠቃላይ ለኑሯቸውና ለእድገታቸው የሚያስፈልጋቸውን ንጥረ - ነገር ብቻ ስይኾን የሰው ጉልበትም አልፎም ለጦርነታቸው ተዋጊነት የነበሩት ከቅኝ ግዛታቅቸው በወሰዱት ነበር።
ይኽን ኹሉ የነፈገቻቸው ኢትዮጵያችን ነች። እንዲህ- እንድዲህ ዓይነቱ ነቀርሳነታቸውን አበዛው አጠነከረብንም። የልጆችዋም የተፈጥሮ ብልህነትና ኩሩነት የበለጠ አስጠላ!
ፈረንጆቹ እስከዚያን ጊዜ አይበገሬዎች - አይደፈሬዎች የነበሩትን እነርሱም ሰዎች መኾናቸውን ረስተው አምላክ በኃይሉ ሲያሳያቸው በጸጋ በመቀበል ፈንታ አቂመው በ፴ ዓመታቸው መጡብን። የሚያሳዝነው መምጣታቸው ብቻ ሳይኾን አመጣጣቸው ነው። ያውም በመንግሥታት ደረጃ የገቡትን ቃልኪዳን አፍርሰው። ( ሊግ ኦቭ ኔሽንዝ )
ሙሶሊኒ ዘልሎ ሊበቀል አልመጣም። በእንግሊዙ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ሆርና በፈረንሳዩ አቻው ላቫል ተገፋፍቶ እንጂ። ሲመጣም የአድዋው እንዳይደገምበት

የዓለም- ዐቀፍ ሕግ የከለከለውን መርዝ እየነነሰነስ… እንደነበር ታውቃላችሁ።፣ የዉሉ አባሎቹ ኹሉ እያወቁ !

አንድዬ የማይጥላት አገር ኹለተኛወኝ የዓለም ጦርነት አምጥቶ እርስ በርሳቸው ሲያባላቸው፣ እንግሊዥ አጋራችን ኾና ለራስዋ ስትል፣ ጣሊያንን ካስወጣን በኋላ አውሮፓ ውስጥ በጀርመን ተይዘው የነበሩትን ከአሜሪካን ጋር ነጻ ያውጧቸውኝ ኹሉ "ነጻ ፈረንሳይ ወዘተ ሲሉ
ኢትዮጵያችንን፦ የነጻነትዋን እመቤት "የተያዠች/የተወረረች የጠላት ግዛት" "ብለው ለ፲፪ ዓመት ተዘፈዘፉባት። መጀመሪያ " ንጉሣችሁን እናመጣላችኋለን !" ብለው ን.ነገሥቱን ግዛታቸው ሱዳን ጠረፍ ላይ አስቀምጠው እነርሱ ሊገቡ ነበር፤፣ ጀግኖችና ብልሆች አባቶቻችን / አርበኞች
"ን. ነግሥታችንን አምጡ! አላበለዚያ እኛ በነጮች መኻል ( ጣሊያን - እንግሊዝ )ያለውን ልዩነት አናውቅም ብለው ሲያፈረጥሙ እነርሱ ቀድመው አዲስ አበባ ገብተው ጃንሆይን በኋላ አስገቧቸው።
አላማቸው ወዳጅ- የጦር ጓደኛ መስለው ገብተው ሊዘረፈጡባት ነበር። በኋላ "አብረን እንግዛ ማለት ፈለጉ ፦ በተንኮላቸው ኹሉ የበለጥ ተንኮል ገጥሟቸው ። ለቀቁ።

እዚህ ላይ ባሰብሁት ቁጥር በደስታ የሚያስፈነድቀኝን፣ ላካፍላችሁ። አንድ ቀን የእንግሊዙ የጦር አዛዥ ለጃንሆይ " ላነጋግርዎት እፈልጋለሁ ብሎ ላከባቸው " አሉ፤፣ ፍላጎቱ እርሱ ዘንድ እንዲሄዱለት ነበር። አባ ጠቅልም " ምን አለ? በሚፈልጉበት ጊዜ ዐቃቤ ሰዓት አስይዘው ሊመጡ ይችላሉ! " ( ቀጠሮ በጸሐፍዬ በኩል ጠይቀው፣ ) አዛዡ ማን እንደኾን አረጋገጥላቸው ይባላል፤

እንደ ደቡብ አፍሪካ በቀለም በአገራችን ሊጫወቱ ፈልገው፣ ሕዝቡ በወንበርና በፍልጥ መብቱን አስከብሯል።

ነገሩ ብዙ ነው። ካገራችን ሲያስወጧቸው ግን ጣሊያን የሠራውን ብዙ የሚጠቅም መሣሪያ እንደ ጀነሬቶር - ወፍጮ መኪናዎች የሚችሉትን ነቅለው ወደ ኬንያ ወሰዱት፦ የማይችሉትን ከጥቅም ውጪ አድርገው አበለሻሹት። እመጨረሻው ላገራቸው የላኩት ውስጥ " አንድም የሚሠራ ነገር አልተውንላቸውም ነበር።
ይህም ብቻ አይደለም፦ ጃንሆይ ሲገቡ ባዋጃቸው ጦረኛ ያልኾኑትንም ጣሊያኖች እንደባንዶች ምሕረት አድርገውላቸው ነበር። ይህም ለታላቅ ዘዴ ነበር። " እባብ ለባብ!" ኾነና እንግሊዞቹ ሞያ ያላቸውን ጣሊያኖች ሙልጭ አድርገው ወደ ኮሎኒያቸው ወሰዷቸው።

ይባስ ብለው የዱር አውሬዎቻችንን ዝቅ ብለው በሚበርሩ አይሮፕላኖች እየነዱ ወደኬንያ ወሰዷቸው።

(በክፍል 3 እስክንገናኝ ቸር ያሰንብተን)